# ይሻላል አልሽ እንዴ?

ይህ ግጥም በቤይሩት ከተማ በጠራራ ፀሐይ በጠገቡ ጎረምሶች እጅ ላይ ወድቃ በጭካኔ እየተገፈተረችና እየተጎተተች፤ እንደ ሰው ሳይሆን እንደማይረባ ቆሻሻ በመኪና ውስጥ የተወረወረችው፤ ከዚያም ምክንያቱ በትክክል ሳይታወቅ ለህልፈተ ህይወት ለተዳረገችው ውድ ኢትዬጵያዊ እህታችን አለም ደቻሳና የእሷ አይነት እጣ ፋንታ ላጋጠማቸው ሁሉ ማስታወሻ ነው።

አገሬ ከስዊድን
20120314

አልሽ እንዴ እህታችን ፤ አልገባም አገሬ
እንቆቅልሽ ሆነ ፤ የአንች አሟሟት ዛሬ
እንዴት ይሆን እቴ ፤ ይሄ የአንች አሟሟት
እራሷን አጠፋች ፤ ተባለ እንደዘበት
ውነት ይሆን እንዴ ፤ የተሰማው ዜና
ተስፋ ቢሱ ኑሮ ፤ አደከመሽና
ባወጣው ባወርደው ፤ ብቋጥር ብፈታ
ተስፋ የሚያስጨብጥ ፤ የሚሰጠኝ ፋታ
ደራሽ ስለሌለኝ ፤ ችግር የሚፈታ
ሞቼ ልገላገል ፤ ቁሜ አልንገላታ ።
አልሽ እንዴ እህታችን ፤ አልገባም አገሬ
እንቆቅልሽ ሆነ ፤ የአንች አሟሟት ዛሬ ።

አለም የአንች ነገር ፤ ሆኖ እንቆቅልሽ
በሰው ህሊና ውስጥ ፤ ሰርጿል ስቃይሽ
ከደከመው ድምፅሽ ፤ ከተሰረቀረቀው
ያወጣሽው ቃላት ፤ የተቆራረጠው
የሰማውን ሁሉ ፤ ጆሮ ያሳቀቀው
ደህንነትሽን እንጅ ፤ ሞትሽን መች ናፈቀው
አልሽ እንዴ እህታችን ፤ አልገባም አገሬ
እንቆቅልሽ ሆነ ፤ የአንች አሟሟት ዛሬ ።

ተስፋ ቢያስቆርጠኝ ፤ በሀገር ላይ ኑሮ
የተሻለ መስሎኝ ፤ ስደት ጋራ ዞሮ
ያው ነዉ አልተሳካም ፤ ስቃይ ነው ሮሮ ።
መከራና ውርደት ፤ ደጋግሞ አጥቅቶኝ
ልጆቸን ማሳደግ ፤ መሳም ተስኖኝ
ሰው መሆኔ አስጠላኝ ፤ ሞት ይገላግለኝ
አልሽ እንዴ እህታችን ፤ አልገባም አገሬ
እንቆቅልሽ ሆነ ፤ የአንች አሟሟት ዛሬ ።

አለም አትለይን ፤ ሁኝን አስተማሪ
በውስጥሽ ያለውን ፤ አውጭው ተናገሪ
ሴት እህቶችሽን ፤ በስደት አማክሪ
ከልምድሽ አካፍይን ፤ ምንም ሳትፈሪ
መቋጫ ቢኖረው ፤ የበርሀው ጥሪ
አልሽ እንዴ እህታችን ፤ አልገባም አገሬ
እንቆቅልሽ ሆነ ፤ የአንች አሟሟት ዛሬ ።

EthioLion.Com

የትኛው ብሶት ነው ፤ ያስቆረጠሽ ተስፋ
ሲጎትቱሽ ይሆን ፤ በግላጭ በይፋ
ወይስ በየቀኑ ፤ ጥጋብ ዘለፋቸው
እርካታን በማያውቅ ፤ በልቅ አመላቸው
በዙሪያ ገባውስ ፤ ምን ተገንዝበሽ
ቋሚ ዋቢ አጣሽ ወይ ፤ የሚደርስልሽ
ለመብትሽ የሚቆም ፤ ወገን ደም መለሽ ።
አልሽ እንዴ እህታችን ፤ አልገባም አገሬ
እንቆቅልሽ ሆነ ፤ የአንች አሟሟት ዛሬ ።

እቴ ያገሬ ልጅ ፤ አለም ታፍነሻል
ስንት አለ በሆድሽ ፤ ሸክም በዝቶብሻል
ይሄን እናውቃለን ፤ ገደሉሽ ሞተሻል ።
ልጅን ያህል ነገር ፤ አደራ ሰጥተሽ
ያልፍልኛል ብለሽ ፤ ከአገር ተሰደሽ
ጠብ ላይል ኑሮ ፤ መከራ ገፍተሽ
እንደከፋሽ ኖረሽ ፤ ወጥተሽ መቅረትሽ
እህቴ እመቤቴ ፤ አለም አጠፋሽ ።
አልሽ እንዴ እህታችን ፤ አልገባም አገሬ
እንቆቅልሽ ሆነ ፤ የአንች አሟሟት ዛሬ ።

EthioLion.Com